# የበላይነትን እንደገና ይንሱ

## ጸሎቶችና አዋጆች

*አባት ሆይ ድንቅ አድርገህ ስለፈጠርከኝ አመሰግንሀለሁ፡፡ ምክንያቱ ደግሞ የፈጠርከኝ አንተ ስለሆንክ ነው፡፡*

*ስለወደድከኝና የአንተ ስላደረግከኝ አመሰግንሀለሁ፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስን የምከተልበትን እድል ስለሰጠኸኝ አመሰግንሀለሁ፡፡*

*የበላይ የመሆንን ፍላጎት በማስተናገዴ ምህረትን አድርግልኝ፡፡ ከሌሎች የተሻለ ሆኖ ለመገኘት ፍላጎቴ በመገዛቴም ይቅር በለኝ፤ እንደ ማንኛውም ሰው ኃጢአተኛ መሆኔን አውቃለሁ፡፡ ያለ አንተም አንዳች ማድረግ አልችልም፡፡*

*የኋላ ታሪኬን በምመለከትበት ጊዜም ሆነ አሁን ባለሁበት ሁኔታ በቡድን ውስጥም ባለኝ ግንኙነት የበላይ ለመሆን ለነበረኝ ፍላጎት ይቅር በለኝ፤ እኔም እክደዋለሁ፡፡ ሁሉም ሰዎች በአንተ ፊት እኩል መሆናቸውን አምናለሁ፡፡*

*ሌሎችን ዝቅ የሚያደርግ ንግግርን በመናገሬ ይቅርታ አድርግልኝ፡፡ ለነዚህ ቃላቶቼ ምህረትን እጠይቃለሁ፡፡*

*በዘራቸው፣ በፆታቸው፣ በሀብታቸውና በትምህርታቸው ምክንያት ሌሎችን ዝቅ አድርጎ ማየትን እቃወማለሁ፡፡*

*በፊትህ መገኘት የቻልኩት በጸጋህ ብቻ መሆኑን አውቃለሁ፡፡ በሰው ልጆች ላይ ሊደረግ ካለሁ ከማንኛውም ፍርድ እራሴን እለያለሁ፡፡ ያዳንከኝን አንተን ብቻ እመለከታለሁ፡፡*

*ጻድቆች የበላይ ናቸው የሚለውን የሙስሊሞች አስተምህሮ እክዳለሁ፡፡ ሙስሊም መሆን ስኬታማ ያደርጋል፣ ሙስሎሞች የበላይ ሕዝቦች ናቸው የሚለውን እክዳለሁ፡፡*

*ወንዶች ከሴቶች የበላይ ናቸው የሚለውን አስተሳሰብ አልቀበልም፡፡ ደግሞም እክዳለሁ፡፡*

*የሰማዩ አባት እግዚአብሔር ሆይ ከነበረኝ ማንኛውም የበላይ የመሆን አስተሳሰብ እመለሳለሁ፡፡ አንተንም ለማገልገል መርጫለሁ፡፡*

*ጌታ ሆይ በሌሎች ስኬት ለመደሰት መርጫለሁ፡፡ በሌሎች ላይ መቅናትና ጥላቻን አልቀበልም ደግሞም እክደወለሁ፡፡*

*ጌታ ሆይ በፊትህ ምን ዓይነት ሰው ስለመሆኔ ጤናማና ትክክለኛውን ፍርድ ስጠኝ፤ እንዴት እንደምታየኝ እውነቱን አስተምህረኝ፡፡ አንተ የምትፈልገው ዓይነት ሰው እንድሆንልህ እርዳኝ፡፡*